# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org




አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

**ግንቦት 7 የፍትህና ዴሞክራሲ ንቅናቄ ዘወትር እንደሚለው ሁሉ ይህ የዜግነትና የሀገር ውርደት፣ ይህ ሁሉ የወገን መከራ የሚቆመው የዚህ ሁሉ መሰረት የሆነው ወያኔና ስርአቱ ከመሰረቱ ሲነቀልና ሲወገድ መሆኑን ላፍታም አይዘነጋውም።**

**ግንቦት 7ን ተቀላቀሉ በያላችሁበት ግንቦት 7 ሁኑ!! እኛ ከዚህ ውርደት ሞቶ የሚገኘው ነጻነት ይሻላል ብለን የተነሳን ልጆቻችሁ ነን። እርሰዎስ?**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ፋሽስት ወያኔ ከምንም በላይ የዜጎቻችን ደህንነት ያሳስበናል በማለት ሹፈት አሰማ

በሳውዲ አረቢያ በወገኖቻችን ላይ በደረሰው በደል አንዴም እንኳ ድምጹን ባለማሰማቱ በያቅጣጫው እየተወገዘ ያለው ፋሽስት ወያኔ፤ ለወገኖቻችን ስቃይ ስሜታችንን ሀዘናችንን እንገልጻለን ብለው በአዲስ አበባ ሳውዲ አረቢያ ኤምባሲ በተሰበሰቡ ወገኖቻችን ላይ የዱላ መአት ያወረደው ፋሽስት ወያኔ ዛሬ ግን ተገልብጦ በወገኖቻችን ደህንነት ላይ ድርድር የለም በማለት ሹፈት እያሰማ መሆኑ ታወቀ።

"ምን ማለት ነው እንዲህ አይነት ንግግር" የሚሉ አንዳንድ ወገኖች "ትላንት መግረፍና መግደል የሳውዲዎች ሉአላዊ መብት ነው ሲሉ የነበሩ ወያኔዎች ዛሬ ምን አዲስ ነገር ተገኘና ነው ስለ ወገን ክብር ሊዘመር የሚሞከረው። ይህ በእርግጥ ካንጀት ነው ካንገት? ዛሬ ምንም ይበሉ ምን ፋሽስት ወያኔ ማን እንደሆነ አንዴ አውቀናል" ይላሉ።

"ደላሎችና ኤጀንሲዎች አሁንስ ተሰማችሁ?" ያለውን የቴወድሮስ አድሃኖምን ንግግር በመውሰድም "የምየን ወደ አብየ" የሚሉት ወገኖች፤ ለደላላዎችና ኤጀንሲዎች መብዛት እንዲሁም ለወገናችን በገፍ መሰደድ ዋናው ምንስኤ ማን ሆነና ነው ጭራሽ መውቀስ የተፈለገው" ይላሉ።

በአገዛዝ ዘመኔ በሙሉ ከፍተኛ እድገትና የኑሮ መሻሻልን አምጥቻለሁ የሚለው ወያኔ ታይቶና ተሰምቶ በማያውቅ መልኩ ድህነትን አስፋፍቷል። በዚሁ ሰቢያም ስራ አጥነት፣ ልመናና ስደት ባህላችን እንዲሆን አድርጓል። ፋሽስት ወያኔ ከሚገባው በላይ አሳደኩት የሚለው የአገልግሎት፣ የግብርናና የምርት ኢንዱስተሪ ለስራ ፈላጊውን ወጣት የስራ ቦታ ለመክፈት በእጅጉ ተቸግሮ ያታያል።


( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )


## በሳውዲ በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ በደረሰው በደል የወያኔ ዝምታ ደጋፊዎቹን ሳይቀር ማስቆጣቱ ተሰማ

እድሜ ከጾታ አቅመ ደካማ ከነፍሰ ጡር ሳይለይ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ላይ በሳውዲ አረቢያ የደረሰውና እየደረሰ ያለውን መከራ ወያኔ ለማውገዝ እንኳ አለመድፈሩ የፋሽስት ወያኔ ደጋፊዎችን ሳይቀር ማስከፋቱ ታወቀ። ከዚህ በፊት በማንኛውም መልኩ የወያኔ ጭፍን ደጋፊ እንደነበር የሚገልጸው ወጣት "አረ ይህ እኮ ልዩ ነው፣ ይህ እኮ በዓለም አቀፍ ሚዲያ ሳይቀር በጉልህና በስፋት የተዘገበ ነው" ይላል። "እና ከዚህ ሁሉ በኋላ ሕዝብን አስተዳድራለሁ እንደሚል አንድ አካል ምንም ማለት አለመቻል በጣም ተስፋ ያስቆርጣል። እስከዛሬ የመጣሁበትን መንግድ ሁሉ እንደገና እንድመረምር ተገድጃለሁ።" የሚለው መረጃችን ያነጋገረው ወጣት "እንኳን ተጎጅዎች የራሳችን ሆነው እያለ ባይሆኑ እንኳ የደረሰው ግፍና በደል እኮ በሰብአዊነት እንኳ መግለጫ የሚያስወጣ ነበር፤ ግን አልተደረገም። በእውነት በወያኔ እጅጉን አፍሬያለሁ" ብሏል።

"ፋሽስት ወያኔን የምደግፈው እኮ ለሀገራችን እና ለሕዝባችን ጥሩ እድገትንና መሻሻልን ሊያመጣ ይችላል በሚል እንጅ በሌላ አልነበረም" የሚለው ሌላው ደጋፊ ደግሞ "ለኛ ለኢትዮጵያዊያን ከዚህ የባሰ አስከፊ ጊዜ ነበር እንዴ? ብሎ ራሱን ከጠየቀ በኋላ "ግን በዚህ ወገኖቻችን ርዳታ በሚፈልጉበት ወቅት፣ የመጨረሻው ጨካኝ እንኳ አንጀቱ ችሎ ሊያልፋቸው በማይችልበት ፈታኝ ጊዜ፤ እኔ የኛ እያልኩ የማሞካሸው ወያኔ አለመታየቱን ሳስብ ምን ለማለት እንደምችል እቸገራለሁ። በእውነት አንጀት ቆራጭ ነገር ነው። ቃላት የለኝም" ብለዋል።

የፋሽስት ወያኔ ቁንጮዎች በየተራ እየወጡ በአረብ ጎረምሶችና ፖሊሶች የዱላ መለማመጃ እየሆነ ስላለው ምስኪን ወገናችን የመውጫ መንገድ ሳይሆን የሳውዲ መንግስት በሀገሩ ሁሉን ለማድረግ ሉአላዊ መብት እንዳለው ለማሳመን ሲደክሙ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም። ይህ በእንዲህ እንዳለ በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ግን በሳውዲ ለሚገኘው ወገኑ በቻለው መልኩ ለመድረስ በከፍተኛ ጥረት ላይ እንደሆነ ተያይዞ ተጠቅሷል።

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## ወያኔ ልዝብ ሰይጣኑን ቴዎድሮስ አድሃኖምን ጠቅላይ ሚኒስቴር ለማድረግ ሩጫዉን ተያይዞታል

የወያኔው ቁንጮ የነበረው ፋሺስቱ ለገሰ ዜናዊ ከሞተ በሁዋላ የጠቅላይ ሚኒስቴርነቱን ቦታ ለስሙ የያዘው የወያኔው አሻንጉሊት ሐይለማርያም ደሳለኝ ቢሆንም ፈሺስቶቹና ጀብደኞቹ የጉጅሌው አባላት የጠቅላይ ሚኒስቴርነቱን ቦታ በይፋ ለመቆጣጠር ቀን ከሌሊት እየሰሩ መሆናቸውን ከውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ለማወቅ ችለናል። ከሰሞኑ ቴዎድሮስ አድሀኖምን ውሸት ልዩ መታወቂያው በሆነው ኢቲቪ በተደጋጋሚ በማቅረብ ለሀገርና ለወገን አሳቢና ተቆርቋሪ በመምሰል እየተሰራ ያለው ድራማ የዚሁ ህውአት የጠቅላይ ሚኒስቴርነቱን ቦታ በይፋ ለመቆጣጠር የሚያደርገው ሩጫ አንዱ አካል መሆኑም ታውቋል። በሳውዲአረብያ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንላይ ለተፈጸመው አሰቃቂ ወንጀል ድምጹን በማጥፋት የተገደሉት ህገወጥ ስደተኞች ናቸው በማለት ለሳውዲ መንግስት ጥብቅና ቆሞ የነበረው የወያኔ ጉጅሌ አገዛዝ በአስገራሚ ሁኔታ ለሀገርና ለወገን ተቆርቋሪ ለመምሰል እያደረገ ያለው ጨዋታ የተለመደው አይነት ወያኔአዊ ድራማ አንዱ አካል ነው ሲል የመረጃ ምንጫችን ጨምሮ ገልጧል።

ሕወሃት በአሁኑ ወቅት ለቀጣዩ ምርጫ ከፍተኛ ዝግጅት እያደረገ ቢሆንም የወያኔን ፋሺስታዊ አገዛዝ በነፍጥ ለማስወገድ በረሀ የገቡ የነጻነት አርበኞች እንቅስቃሴና በህዝብ ዘንድ እያገኙ የመጡት ከፍተኛ ተቀባይነት እንቅልፍ ስለነሳውና እጅጉን ስላስጨነቀው የህዝቡን ስሜት ለመስረቅና ለመግዛት የሚያመች እንቅስቃሴ ለማድረግ በዝግጅት ላይ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል። በያዝነው ወር መጀመርያ አካባቢ ላይም የግንቦት 7 ህዝባዊ ሀይል አመራር አባላትን ለማስገደል ያደረገው ሙከራም በህዝባዊ ሀይሉ የመረጃና የደህንነት ክፍል ከፍተኛ ክትትል ሊከሽፍና በቁጥጥር ስር ሊውል መቻሉም አይዘነጋም።

## በጅጅጋ የብሄር ብሄረሰቦችን ቀን ለማድመቅ የተቀረጸው የመለስ ዜናዊ ሃውልት እንዲፈርስ ታዘዘ

ወያኔ በየአመቱ በህዳር ወር የኢትዮጵያን ብሄር ብረሰቦች ሰብስቦ የሚያስጨፍራቸዉን ቀን ለማስታወስ የዘንድሮዉ ባለተራ የሆነችዉ ጅጅጋ በዐሉን ለማክበር አለፈቀዷና አለፍላጎቷ ሽር ጉዱን ተያይዛዋለች። የኦጋዴን ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዋና ከተማ የሆነችዉ ጅጅጋ 8ኛውን የብሄር ብሄረሰቦች ቀን ታከብራለች መባሉን ተከትሎ ከተማዋ በወያኔ ባለስልጣኖችና በልማታዊ አርቲስቶች ጋጋታ ቁም ስቅሏን እያየች መሆኗን ዘጋቢዎቻችን ከስፍራዉ የላኩልን ዜና ያስረዳል። ይህንኑ የወያኔ የይስሙላ በአል ለማዳመቅ ተብሎ ህዝብ ተገላገልኩት ብሎ የረሳዉንና የዘረኝነት ምሶሶ የነበረዉን መለስ ዜናዊን ለማስታወስ 243 ሺ ብር የህዝብ ገንዘብ ወጪ ሆኖበት የተሰራዉ የዘረኛዉ መሪ ሃዉልት ፈጽሞ ከቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ምስል ጋር የማይመሳሰልና በመልክም ሆነ በቁመትና ቁመናዉ የማይገናኝ ነዉ ተብሎ ስለታመነበት እንዲፈርስ ትዕዛዝ ተላልፏል። የሃዉልቱ መሰራትና እንዲፈርስ መወሰኑ ብዙ የፌዴራል ባለስልጣኖችን ያስቆጣ ሲሆን አሁንም ድረስ ብዙዎችን እያናገረ መሆኑን ለማወቅ ተችላል። የክልሉ ባለስልጣናት ሃውልቱ የተሸፋፈነበትን ሸራ ገልጠዉ ለባለስልጣናቱ ማሳየት ሲጀምሩ ከፌደራል መንግስቱ ባለስልጣናት በደረሰባቸው ከፍተኛ ትችት ወዲያውኑ የተገለጠዉ ሸራ ተመልሶ እንዲሸፍ አድርገዋል። ሸፍነው አፍርሰውታል። አአንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ሀውልቱ ከመለስ ይልቅ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስን ይመስላል እያሉ የተሳለቁ ሲሆን የፈረደበት ሃዉልቱን የቀረፀዉ ግለሰብ በቁጥጥር ስር ውሎ ካለፉት ሶስት ሳምንታት ጀምሮ በእስር ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል።


( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )


## ግንቦት7 እና አክራሪ ኃይሎች ፓርላማውን ተቆጣጥረዉ ሊጎዱን ይችላሉ ሲልየፌደራል ጉዳዮች ሚኒስተር ፍራቱን ገለጸ

የግንቦት 7 ንቅናቄና በሐይማኖት ሰም የሚንቀሳቀሱ አክራሪ የእስልምና ኃይሎች በ2007ቱ ምርጫ በኢህአዴግ አባላት ስም ፓርላማዉን በመቆጣጠር ኢህአዴግን ሊጎዱት ይችላሉ ሲል የፌዴራል ጉደዮች ሚኒስትሩ ሽፈራው ተክለማርያም ተናገረ። ሽፈራው ተክለማርያም ይህንን የተናገረዉ "በክርስትናና በእስልምና ሃይማኖት ሽፋን የሚካሄደው የፖለቲካ እንቅስቃሴ የመንግስት ቀጣዩ የምርጫ ፈተና" በሚል ርእስ ለኢህአዴግ ከፍተኛ አመራሮች ባቀረበዉ ጽሁፍ ነው። የሽፈራው ተክለማርያምን ሙሉ ንግግር የያዘዉ ሰነድ እጄ ላይ አለ የሚለዉና ዜናዉን የዘገበዉ የኢትዮጵያ ሳቴላይት ቴሌቪዥን በሰነዱ ግርጌ ላይ "ለመደበኛ አባላት የማይነገር፣ ለከፍተኛ አመራሮች ብቻ" የሚል ማስጠንቀቂያ እንደተጻፈበት ተናግሯል።


( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

# የህዝባችን መከራ የወያኔ የፖለቲካ መጠቀሚያ አይሆንም!

በሳውዲ አረቢያ ውስጥ እጅግ ብዙ ኢትዮጵያውያን አሁንምመከራና ስቃይ ላይ ናቸው። የደረጃ ጉዳይ ነው እንጂ ችግሩ በመካከለኛው ምስራቅ ሀገሮች በሚኖሩ ወገኖቻችን ላይ የተንሰራፋ ነው። በመላው አለም ተበትኖ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ካለማቋረጥ ያደረገው ወገንና ሀገር አኩሪ ጩኸትና አቤቱታ ችግሩ በአለም ዙሪያ ትኩረት እንዲያገኝ ባያደረግ ኖሮ የወገኖቻችን መከራ ከዚህም በከፋ መልክ ይቀጥል እንደነበር ጥርጥር የለውም። አንድ ቀን እንኳን ለሚገዛው ህዝብ ሀላፊነትና ተጠያቂነት ተሰምቶት የማያውቀው የወያኔ ጉጅሌ መንግስት እግሩን እየጎተተ ቢሆንም ወደ ችግሩ አቅጣጫ እንዲመለከት የተገደደው በዚሁ የወገን ጩኸት መሆኑ ግልጽ ነው።

ወያኔ ስላልቻለ ነው እንጂ ይህንን ከአለም አጽናፍ እስከ አለም አጽናፍ ያስተጋባ የወገን ደራሽ ድምጻችንን አዲስ አበባ ላይ እንደ አደረገው በሃይል ለማፈን ወደኋላ አይልም ነበር።

ሀፍረት የለሾቹ የወያኔ መንግስት ባለስልጣኖች ይህን የተጋለጠ ሀገርና ህዝብ አዋራጅ ተግባራቸውን እና በውሸት የተበከለ ገመናቸውን ለመሸፈን ከዚያም አልፈው የዋሆችን በማታለል የፖለቲካ ትርፍ ለማትረፍ የተለመደ ቲያትር መስራቱን ተያይዘውታል። ቴዎድሮስ አድሃኖም ችግሩ ባለበት በሳውዲ መሬት ላይ ሳይሆን የሳውዲ አረቢያ መንግስት በራሱ ወጪ አሳፍሮ ቦሌ አውሮፕላን ጣቢያ ባፈሰሳቸው ኢትዮጵያውያን መሃል እየተጎማለለ ያዛኝ ቅቤ አንጓች ቲያትሩን ሲሰራ ትንሽ እንኳን ሀፍረት አይታይበትም።

እነዚሁኑ ወደ ሀገር የተመለሱ አእምሯቸው በችግር የተመሰቃቀለ ዜጎች ወደ ካሜራ እየገፉ ስለ ሳውዲ ኤምባሲያቸውና ስለመንግስታቸው ‘ድንቅ” አገልግሎት እንዲናገሩ ያስጠኗቸውን ተመሳሳይ አረፍተ ነገር መስማት የሚያሳዝን ባይሆን ኖሮ ተወዳዳሪ የሌለው ኮሜዲ ይወጣው ነበር።

እውነቱ ዛሬ በሀገራችን የሰፈነው ስደትና አብሮት የሚመጣው መከራ ሁሉ ዋናው አምራች ፋብሪካ ወያኔ መሆኑ ነው። ወያኔ የገነባው ጥቂት ጀሌዎቹንና ሎሌዎችን ተጠቃሚ ያደረገና አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በተለይ ወጣቱ በሀገሩ ተስፋ እንዲቆርጥ ያደረገው ስርአት ነው። የስደታችንና የመከራችን ምንጭ ስደት የሚመጣው በሀገር ተስፋ መቁረጥ ነው። እንጀራ ፍለጋና ጭቆናና አፈና ሸሽት አምልጠን በየባዕድ ሀገሩ እንድንከራተት የሚያደርገን የወያኔ ስርአት ነው። በታሪካችን ውስጥ ተሰደን በባዕድ የተዋረድነው በወያኔ ምክንያት ነው።

በሀገር ውስጥ በአፈና ስር ሆናችሁ፣ በውጪው አለምም በየኢምባሲው የምታሰሙት ጩኸትና የምታፈሱት እምባ እብሪትና ትእቢት ያደነደነውን፣ ዝርፊያ ያደነዘዘውን የወያኔን ልብ እንደማያሸብረው ማወቅ አለብን።

የወያኔ ሹማምንቶች ይግረማችሁ ብለው ከአላንዳች ሀፍረት ያውም በሳውዲ አረቢያ ወጪ ተጓጉዘው ሀገር የገቡትን ግራ የተጋቡ ስደተኞች ለፖለቲካቸው ማሳመሪያ በቴሌቪዥን ስእልና ፎቶግራፍ መነሻ ሲያደርጉትና ለፖለቲካ ስራ መሳሪያ ሲያውሉት እያየን ነው። በነሱ ቤት ብልጥ ፖለቲከኞች መሆናቸው ይሆናል። በኛ ቁስል ላይ እንጨት እየሰደዱ መሆናቸውን ግን ፈጽሞ አይሰማቸውም።

ወያኔ በመካከለኛው ምስራቅ ተሰደው ለፍተው የሚኖሩት ወገኖቻችን በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ያውቃል። ቢያንስ በየኢምባሲው ያስቀመጣቸው ነጋዴዎች ይነግሩታል። ችግሩን እንዳላየና እንዳልሰማ የሚያየው ከዜጎች ይልቅ እነሱ አፈር ግጠው ለፍተው ለሚያመጧት የውጪ ምንዛሬ የበለጠ ፍቅር ስላለው ነው። በዚህ ተግባሩ ወያኔ ወገኑን የሸጠ ባሪያ ፈንጋይ ነጋዴ እንጂ የመንግስት መሪ መሆኑ ያጠራጥራል።

ግንቦት 7 የፍትህና ዴሞክራሲ ንቅናቄ ዘወትር እንደሚለው ሁሉ ይህ የዜግነትና የሀገር ውርደት፣ ይህ ሁሉ የወገን መከራ የሚቆመው የዚህ ሁሉ መሰረት የሆነው ወያኔና ስርአቱ ከመሰረቱ ሲነቀልና ሲወገድ መሆኑን ላፍታም አይዘነጋውም።

እንባችን የሚደርቀው ደማችን በየቦታው መፍሰሱ የሚቆመው መብታችን እንደዜጋ ተከብሮ ቀና ብለን የምንሄድበት ሀገር በትግላችን የተቀዳጀን ጊዜ ብቻ ነው።

ግንቦት 7ን ተቀላቀሉ በያላችሁበት ግንቦት 7 ሁኑ!! እኛ ከዚህ ውርደት ሞቶ የሚገኘው ነጻነት ይሻላል ብለን የተነሳን ልጆቻችሁ ነን። እርሰዎስ?

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

## ታላቁ ሩጫ በአድማቂዎች ሳይሆን መሳሪያ ባነገቡ ወታደሮች ታጅቦ ተካሄደ

ለወትሮዉ ብዙ ህዝብ ዉድድሩን ለማየት ብቻ ሳይሆን ተቃዉሞዉን ለማሰማት በስፋት የሚሳተፍበት “ታላቁ ሩጫ” ዘንድሮ ለዛዉንና የዉድድር መንፈሱን አጥቶ የጦር ሜዳ መሳሪያ ባነገቡ የወያኔ ወታደሮች ተከብቦ ባለፈዉ እሁድ ህዳር 15 ቀን 2006 አዲስ አበባ ዉስጥ መካሄዱን ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። መነሻውን ጃንሜዳ በማድረግ ፥ በ6 ኪሎ አደባባይ ፣ በምኒሊክ ሆስፒታል፣ በቀበና ፣በአቧሬ ፣ በእንግሊዝ ኤምባሲና በመገናኛ አደባባይ በማደረግ ተመልሶ ጃንሜዳ የተጠናቀቀው ይህ ለ 13ኛ ጊዜ የተካሄደው ውድድር ከወትሮው በተለየ ጥበቃና የፖሊስ ተደጋጋሚ ፍተሻ በመታጀብ ነበር።የእሁዱ ዉድድር ከመካሄደ በፊት በዋዜማዉ ቅዳሜ ህዳር 14 ቀን የህጻናት የታላቁ ሩጫ ውድድር እንደሚካሄድ በመገናኛ ብዙኋን የተነገረ ቢሆንም ዉድድሩን ለማካሄድ መርሃግብሩ ከተጠናቀቀ በኋላ ዝግጅቱ ሊካሄድ ጥቂት ሰዓታት ሲቀሩት የሽብር ጥቃት ሊፈጸም ይችላል በሚል ፍርሀታ መሰረዙም ታውቋል።

ታላቁ ሩጫ ከመመሩ በፊት እሁድ ማለዳዉ ላይ ህዝብ ወደ አደባባዮች የሚገባባቸዉን ቦታዎች ተዘዋውሮ ተመለከተው ሪፖርተራችን በላከልን ዜና መሰረት ከአራት ኪሎና ከስድስት ኪሎ የመጡ ተሳታፊዎች በሶስት የተለያዩ ስፍራዎች ተደጋጋሚ ፍተሻዎች አንደተደረገባቸውና የተለያዩ ድርጅቶች ዓርማዎችንና ሌሎች አልባሳት የያዙ ተወዳዳሪዎች ወደውድድሩ ቦታ ለማለፍ ከፍተኛ ችግር እንዳጋጠማቸዉ ማየቱን ተናግሯል። ሰማያዊ ፓርቲ በዚህ ውድድር ላይ ጥቁር ልብስ በመልበስ በሳዑዲዓረቢያ በወገኖቻችን ላይ የደረሰውን ችግር ሕዝቡ እንዲቃወም ያቀረበውን ጥሪ ተከትሎ ፖሊሶች በተለይ ጥቁር አልባሳት ያደረጉ ሰዎችን ልብስ ሲያስወልቁ ታይተዋል። በተጨማሪም ከስድስት ኪሎ ውድድሩ እስከሚጀመርበት ጃንሜዳ ድረስ የሚገኙ ማናቸውም የንግድ ሱቆች፣ መኖሪያ ቤቶች፣የተለያዩ ቢሮዎች፣ የህክምና ማዕከላትና የመሳሰሉት እንዲዘጉ በፖሊሶች በመገደዳቸው ተወዳዳሪዎች ከመደብሮች ውሃና ለስላሳ መጠጦችን ለመግዛት ሳይችሉ ቀርተዋል። ከ37 ሺህ በላይ አንጋፋና ታዋቂ አትሌቶችን ጨምሮ የግል ተወዳዳሪዎች ተካፋይ የሆኑበት ይህው ውድድር በፖሊስ በኩል የተፈራው የሽብር ጥቃት ሳይገጥመው በሰላም ተጠናቆአል።

## ሳዐዱ አረቢያ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ላይ የሚፈጸመው ጥቃት እንደቀጠለ ነው

ሳዑዲ አረቢያ ዉስጥ ስትርሀ እየተባሉ በሚጠሩ የማጎሪያ ካምፖች ውስጥ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ህጻናት፤ ወጣቶች፤ አረጋዉያንና ታማሚዎች በከፍተኛ ችግር ላይ እንደሚገኙ ከወደ ሳዑዲ የሚመጡ ዜናዎች አስረዱ። በካምፖቹ ዉስጥ የሚገኙት ኢትዮጵያዉያን በዉኃና ምግብ እጥረት አሁንም የሚደርስላቸዉ አጥተዉ የሚሰቃዩ ሲሆን ከካምፑ ወጣ ብለዉ ለራሳቸዉና ለቤተሰቦቻቸዉ ምግብ እና ውሀ ለመግዛት የሚሞክሩ ሰዎች በሳዑዲ ፖሊሶች እንደሚገደሉ ጓደኞቻቸው የተገደሉባቸው የተገደሉባቸዉ ኢትዮጵያውያን ለዘጋቢዎቻችን በላኩት ዜና ገልጸዋል። አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙት ዘጋቢዎቻችን ደግሞ ከሳዑዲ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱት ወገኖቻችን በአይ ኦ ኤም ወጪ ህክምና እየተሰጣቸው ሲሆን ብዙዎች በአካል ጉዳትና በስነልቦና ችግር እየተሰቃዩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በርካታ ተስፋ የቆረጡ ኢትዮጵያውያን ከተጠለሉባቸዉ ካምፖች ዉስጥ ግንብ እየዘለሉ መዉጣት መጀመራቸዉ ታወቀ። በተለይ መዲናህ ከተባለ መጠለያ ካምፕ ዉስጥ እየዘለሉ በአካባቢዉ ወደሚገኘዉ ታይባን ዩኒቨርስቲ ካምፓስ እንደገቡ የአገሪቱ ፖሊስ አስታውቋል። ብርጋዴር ፋህድ ቢን አሚር አል ጋናም የተባሉ የፖሊስ ቃል አቀባይ እንደገለጹት 15 ኢትዮጵያውያን ወደ ዩኒቨርስቲው ግቢ የገቡ ሲሆን የጸጥታ ሀይሎች ኢትዮጵያውያኑን በመያዝ ወደ ማጎሪያ ካምፓቸው የመለሷቸዉ ሲሆን ሁኔታዉ በፈጠረዉ ግርግር የተነሳ ታይባህ ዩኒቨርሲቲ መዘጋቱም ታዉቋል። ኢትዮጵያውያኑን ያስቆጣዉ አስቸጋሪ የሆነዉ የካምፑ ኑሮና ወደ አገራቸው ለመመለስ ቪዛ የማግኘቱ ሂደት ስለዘገየባቸው እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

በሌላ በኩል ደግሞ የሳዑዲ መንግስት በኢትዮጵያውያን ላይ የሚፈጽመውን ግፍ ለመቃወም የሚደረጉ ሰልፎች ቀጥለዋል። በስዊድን የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ረቡእ እለት በኢትዮጵያ ኢምባሲ ፊት ለፊት የተቃውሞ ሰልፍ በማድረግ የሳውዲን ንጉስ ፎቶ ግራፍ አቃጥለዋል። ሀሙስ እለት ደግሞ በስፔን የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ማድሪድ በሚገኘው የሳወዲ ኢምባሲ ፊት ለፊት የተቃውሞ ሰልፍ አድርገዋል። ኢትዮጵያውያኑ አቤቱታቸውን ለሳውዲ ኢምባሲ ተወካይ ማቅረባቸውም ታውቋል;፡ከአዲስ አበባ በሚደርሱን ዜናዎች መሰረት የወያኔ አገዛዝ አዲስ አበባ ለሚመለሱ ወገኖቸችን ምን አይነት ድጋፍ እንደሚያደርግ ለማወቅ አለተቻለም። የዝግጅት ክፍላችን ስልክ ደዉሎ ያናገራቸዉ አንዳንድ የተመላሽ ስደተኞች ቤተሰቦች በሰጡን አስተያየት ለወገኖቻችን መመለሻ ገንዘብ የከፈሉት አይ ኦ ኤምና የሳውዲ መንግስት ናቸዉ፤ አገር ቤት ከገቡ በኋላ ደግሞ የምንከባከባቸዉ እኛዉ ነን፤ የነ ቴዎድሮስ አድሃኖምና የሌሎች የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣኖች ድርሻ ከተመላሾች ጋር ፎቶ ግራፍ መነሳት ነዉ ብለዋል።

# ቴዎድሮስ አድሃኖም ቢያጥቡት የማይጠራ ወያኔ ነዉ

የኢትዮጵያ ህዝብና እናስተዳድረዋለን የሚሉት አምባገነን ገዢዎቹ ተስማምተዉና አንዱ ሌላዉን አክብሮ የኖረበት አንድም የታሪክ አጋጣሚ የለም። የእስከዛሬዉ ታሪካችን ምዕራፍ በጥቅሉ ሲታይ ታሪካችን የሚቋጨዉ ህዝብ ተረገጠ፤ ተጋዘ፤ ገዢዎች ደግሞ ረገጡ፤ ገዙ፤ አሰሩ፤ አጋዙ እየተባለ ነዉ። አዎ! የኢትዮጵያ ህዝብ እስከዛሬ ባለዉ ታሪኩ ተግዟል፤ ተረግጧል፤ ተንቋል፤ ተንቋሿል። የዘንድሮዉ በተለይ ባለፉት ሁለትና ሦስት ሳምንታት እየደረሰብን ያለዉ ብሄራዊ ዉርደትና ንቀት ግን ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቅ ልዩ ከልዩም ልዩ ነዉ። በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዘመን የኢትዮጵያ ህዝብ ልክ እንደዛሬዉ ሰብዓዊ መብቱ ተረግጧል፤ ፍትህ ተነፍጓል፤ ነጻነቱን ተገፍፏል፤ ሆኖም አገር ዉስጥም ከአገር ዉጭም ፈላጊና ባለቤት አንደሌለዉ የቤት ዉስጥ እንስሳ የወገንም የባዳም እጅ አልተረባረበበትም። አንገፍግፎን አንፈልግም በቃ ብለን ያስወገድነዉ የቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ስርዐት በስልጣን ላይ በነበረበት ግዜ "ኢትዮጵያ" የሚለዉ ስምና "ኢትዮጵያዊነት" አገር ዉስጥም ሆነ አዉሮፓ፤ አሜሪካና አፍሪካ ዉስጥ እጅግ በጣም የተወደደና የተከበረ ስም ነበር። ዛሬ ወያኔ ነጻ አወጣኋችሁ፤ እኩልነት አመጣሁላችሁ እያለ በሚሰብክበት ዘመን ግን የኢትዮጵያ ህዝብ አገር ዉስጥም በዉጭ አገሮችም ባለቤት አንደሌለዉ ፈረስ ማንም የሚጋልብበት ፈላጊ እንደሌለዉ ዕቃ ያገኘ ሁሉ እንዳሰኘዉ እጁን የሚያሳርፍበት የተናቀ ህዝብ ሆኗል። ለመሆኑ ለምንድነዉ ኢትዮጵያዊነት እንደዚህ እንደ ተራ ዕቃ የቀለለዉ? ኢትዮጵያዉያንስ ለምንድነዉ በየሄዱበት እንዲህ አይነት ዉርደትና ስቃይ የሚደርስባቸዉ? መልሱ ቀላል ነዉ። "ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ" ወይም "ባለቤቱ ያቀለለዉን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለዉም" ነዉ።

የወያኔ አገዛዝ እኛ ኢትዮጵያዉያን "ኢትዮጵያዊነት" እያልን ስለምንሳሳለትና ስለምንከባከብለት ትልቅና ክቡር ሀሳብ በፍጹም ግድ የለዉም። እንዲያዉም ወያኔ ሽንጡን ገትሮ ከሚታገላቸዉ ዋና ዋና ብሄራዊ እሴቶቻችን ዉስጥ "ኢትዮጵያዊነት" የመጀመሪያዉ ነዉ። ስለዚህም ነዉ ባለፉት ሃያ ሁለት አመታት በግልጽ እንደተመለከትነዉ "ኢትዮጵያዊነት" ብለዉ የተጣሩ፤የጮሁ፤ ህዝብን ያስተማሩና የታገሉ ግለሰቦች በወያኔ እየተለቀሙ የታሰሩትና የተገደሉት። ከአገር ዉጭም ቢሆን በየዉጭ አገሩ የሚገኙት የወያኔ ኤምባሲዎች ኢትዮጵያዉያን ከአገራቸዉ ዉጭ ማግኘት የሚገባቸዉን የዜግነት አገልግሎት የሚሰጡት ዜግነታቸዉን እያዩ ሳይሆን ቦንድ የገዛ ያልገዛ፤ "ልማታዊዉን መንግስት" የደገፈ ያልደገፈ እያሉ ወይም "የወርቃማዉ ዘር" አባልነቱን እያጣሩ ነዉ። እነዚህንና ሌሎችም እነዚህን የመሳሰሉ ሰንካላ የወያኔ መስፈርቶች ያላሟሉ ኢትዮጵያዉያን አገር ዉስጥም ከአገር ዉጭም ወያኔ በዜግነት ሳይሆነ በጠላትነት የሚመለከታቸዉ ሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃ ዜጎች ናቸዉ። ዛሬ ከአፍሪካ፤ ከኢሲያና ከላቲን አሜሪካ አገሮች ስራ ፍለጋ ሳዑዲ አረቢያ ከሄዱ ዜጎች ዉስጥ እንደ ኢትዮጵዉያን እጁንና እግሩን ታስሮ የተገረፈ፤ እንደሴቶቻችን በሳዑዲ ጎረምሶች የተደፈረና እንደ ኢትዮጵዉያን በየአደባባዩ የተገደለ የሌላ አገር ዜጋ የለም። ሳዑዲ አረቢያ ዉስጥ የሚገኙ የሌሎች አገሮች ኤምባሲዎች የዜጎቻቸዉ መብት በሳዑዲ መንግስትና ህዝብ ሲደፈር ለምን ብለዉ ይጠይቃሉ ወይም ለዜጎቻቸዉ ግዜያዊ መጠለያ፤ የህክምና እርዳታና የህግ ሽፋን ይሰጣሉ እንጂ ኤምባሲያቸዉ በራፍ ላይ "ዝግ ነዉ" የሚል ጽሁፍ አይለጥፉም።

የወያኔ ኤምባሲ ግን ከስረ መሠረቱ የተቋቋመዉ የወያኔን የራሱን እንጂ የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅም ለማስጠበቅ ስላልሆነ ይህንን የሌሎች አገሮች ኤምባሲዎች ለዜጎቻቸዉ የሚያደርጉትን ጥበቃና እንክብካቤ ለወገኖቹ ለማድረግ አልታደለም፤ ፍላጎቱም የለዉም። ይህንን ቅሌትና ዉርደት ደግሞ ባለፉት ሁለትና ሦስት ሳምንታት በግልጽ ተመልክተናል። ጂዳና ሪያድ ዉስጥ በዜጎቻችን ላይ የሚደርሰዉን መከራና በደል ተቃዉመዉ ሠልፍ የወጡ ኢትዮጵያዉያን በሳዑዲ ፖሊሶች ታድነዉ እንደታሰሩ ሁሉ አዲስ አበባ ዉስጥም በወንድሞቻችንና እህቶቻች ላይ እንዴት እንዲህ አይነት በደል ይፈፀማል ብለዉ ሳዑዲ ኤምባሲ ፊት ለፊት ሠላማዊ ሠልፍ የወጡ ኢትዮጵያዉያን በአረመኔዎቹ የወያኔ ፖሊሶች ታድነዉ ታስረዋል፤ተደብድበዋል። አዎ! ኢትዮጵያዉያን ሳዑዲ ዉስጥም ኢትዮጵያ ዉስጥም ለምን የሳዑዲን መንግስት ተቃወማችሁ ተብለዉ በሁለቱም አገር ፖሊሶች እየታደኑ ታስረዋል ተደብድበዋል።

ከወያኔና ከጥቂት ሆድ አምላኪ ደጋፊዎቹ ዉጭ በአገር ዉስጥና በመላዉ ዓለም የሚገኘዉ ኢትዮጵያዊ በአንድ አላማ ዙሪያ የተሰባሰበበትና አንድ ሳምንት ሙሉ አንድ ቃል በአንድ ትንፋሽ የተነፈሰበት ግዜ ቢኖር ወርሃ ህዳር 2006 የመጀመሪያዉ ነዉ ማለት ይቻላል። የአንድ አገር ህዝብ በአንድ አላማ ስር ሲሰባሰብና በአንድነት ሲቆም ከማንም ከምንም በላይ በዚህ አንድነት መጠቀምም መደሰትም ያለበት መንግስት ነዉ። ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ የወያኔ አገዛዝ ግን ዕቅዱና ስራዉ ሁሉ የኢትዮጵያን ህዝብ ማስጨነቅና ማበሳጨት ነዉ እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ በሚሰራዉ ስራ ተደስቶ አያዉቅም፤ ለወደፊትም የሚደሰት አይመስልም። ከሰሞኑ ሳዑዲ አረቢያ ዉስጥ በኢትዮጵያዉያን ወገኖቻችን ላይ የደረሰዉ ልክ የሌለዉ ስቃይና መከራ መላዉን የኢትዮጵያ ህዝብ ቀፎዉ እንደተነካ ንብ ከዳር ዳር ሲያስቆጣ ወያኔና ሞራለ ብልሹ ሹማምንቶቹ ግን ከዚህ ወገኖቻችንን በባዕድ አገር ለከፍተኛ ጥቃት ካጋለጠና ብሄራዊ ዉርደት ካከናነበን ክስተት ትርፍ ለማግኘት የፖለቲካ ቁማር እየተጫወቱ ነዉ። ኢትዮጵያዉያን ሳዑዲ ዉስጥ በአሰሪዎቻቸዉ፤ በመንደር ዉስጥ ጎረምሶችና በፖሊስ ከፍተኛ ድብደባ፤ እንግልትና ዉርደት ሲደርስባቸዉ ኤምባሲዉ በራፍ ላይ "ኤምባሲዉ ዝግ ነዉ" የሚል ጽሁፍ በመለጠፍ ይበላችሁ እያለ አፉን ዘግቶ የተመለከተዉ የወያኔ አገዛዝ ዛሬ የወገን አሳቢና ተቆርቋሪ ለመመሰል የጭቃ ዉስጥ እሾኩን ቴዎድሮስ አድህኖምንና የአገዛዙን የዉሸትና የቅጥፈት ቃል አቀባይ ዲና ሙፍቲን በግምባር ቀደምትነት በማሰለፍ የፖለቲካዉን ገደል ቁልቁል ተያይዘታል።

ቴዎድሮስ አድሃኖም ቢከፋም ቢለማም የአገሪቱ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስትር ነዉ፤ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስትር የስራ ሀላፊነት ደግሞ አገሪቱንና ዜጎቿን ከዉጭ አገሮች ጋር በሚያገኛኙ ጉዳዮች ላይ ማተኮር ነዉ እንጂ በአገር ዉስጥ የሚሰራዉ ይህ ነዉ ተብሎ የሚነገር ስራም ሀላፊነትም የለዉም። አንዴ ወዳጅ አንዴ ጠላት እየመሰለ እንደ እስስት መልኩን የሚቀያይረዉ ቴዎድሮስ አድሀኖም ግን ሳዑዲ ዉስጥ ድረስልን ብለዉ ሲጣሩት ፊቱን ያዞረባቸዉ ኢትዮጵያዉያን አዲስ አበባ ሲመለሱ ያሉበት ቦታ ድረስ በመሄድ እንኳን ደህና መጣችሁ ለማለት ሲሞክር ይታያል። ሳዑዲ አረቢያ ዉስጥ የሚገኙትን የኢትዮጵያ ኤምባሲና ቆንስላ ጽ/ቤቶች ቅርቅር አድርጎ ዘግቶ የወገን ያለህ ብለዉ የመጡትን ኢትዮጵያዉያን እንጃላችሁ ብሎ ፊቱን ያዞረባቸዉ የአዛኝ ቅቤ አንጓቹ ቴዎድሮስ አድሃኖም እነዚሁኑ እንደ ባዳ ፊቱን ያዞረባቸዉን ኢትዮጵያዉያን አገር ቤት ሲመጡ "እንኳን ደህና መጣችሁ" ማለቱ የገደለዉን ወታደር ለማከም ከሞከረዉ የናዚ ጀርመን ወታደር ተለይቶ የሚታይ አይደለም። ቴዎድሮስ አድሀኖም እንደ ፈረስ ገርተዉ ለዚህ ባደረሱት በነመለስ ዜናዊና ስብሐት ነጋ ጭቅላት ሳይሆን በራሱ ጭንቅላት የሚያስብ ሰዉ ቢሆን ኖሮ የሱ የስራ ድርሻና ሀላፊነት ዜጎቻችን አገር ቤት ከገቡ በኋላ ሳይሆን ሳዑዲ ዉስጥ እያሉ ነበር።

ዛሬ ቴዎድሮስ አድሃኖምም ሆነ ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ከሳዑዲ በሚመለሱት ወገኖቻችን ዙሪያ የሚያደርጉት ልታይ ልታይ የፎቶ እሽቅድምድም ወገኖቻችንን ለመርዳት ሳይሆን ዘረኛ መሪያቸዉ መለስ ዜናዊ ሲሞት ሳያስቡት በድንገት ከእጃቸዉ የወጣዉን የጠቅላይ ሚኒስትርነት ቦታ መልሰዉ እጃቸዉ ለማስገባት ወይም በሚቀጥለዉ አመት በሚደረገዉና ወያኔ ከወያኔ ጋር በሚወዳደርበት ትርጉም የለሽ ምርጫ የፈረደበት ኃ/ማሪያም ደሳለኝን በቴዎድሮስ አድሃኖም ለመተካት ነዉ። አዎ! ለመተካት . . . ለመተካካት። ወያኔ መተካካት እያለ አንዱን ጌኛ በሌላ ጌኛ በልቶ የጠገበዉን አህያ በተራበ አህያ መተካት ከጀመረ ዉሎ አድሯል። የአሁኑም ሩጫቸዉ ቢጭኑት አልሸከም ቢቀመጡበት አልመች ያላቸዉን ኃ/ማረሪያም ደሳለኝን የራሳችን ሰዉ ብለዉ በሚጠሩት በቴዎድሮስ አድሃኖም ለመተካት ነዉ (ኃይለማሪያምማ አሁንስ ቢሆን በቁሙ አልተተካም ብላችሁ ነዉ . . . ድፍን አበሻ ዉጭ አገርም አገር ዉስጥም ሲተራመስ ኃ/ማሪያም አንዲት ቃል አልተነፈሰምኮ)። ሳዑዲ ዉስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያዉያን ወንድሞቻችን ፓስፖርታቸዉን ሲቀሙ፤ ሲደበደቡ፤ሲታሰሩና ሲገደሉ ቴዎድሮስ አድሀኖም የሰጠዉ ምላሽ ቢኖር የኤምባሲዉንና የቆንስላ ጽ/ቤቶችን በር መዝጋት ነበር። አዎ መዝጋት። ልክ ከ1997ቱ ምርጫ በኋላ ከመለስ ዜናዊና ከአግዓዚ ነብሰ ገዳዮች የጥይት እሩምታ ለማምለጥ ወደ ቤተክህነት ጽ/ቤት ግቢ ሸሽተዉ ለመግባት በሞከሩ ወጣቶችና ህፃናት ላይ አባ ጳዉሎስ በሩን እንደዘጉባቸዉ ዛሬም የአባ ጳዉሎስ ታናሽ ወንድም የሆነዉ ቴዎድሮስ አድሃኖም በባዕድ አገር ዉስጥ አድነን ብለዉ በተጠጉት ወገኖቻችን ላይ የኤምባሲን በር ቀርቅሮባቸዋል።

ለመሆኑ ቴዎድሮስ አድሃኖም በየአመቱ ከ40ሺ በላይ ኢትዮጵያዉያን ወጣቶች በለጋ ዕድሜያቸዉ ከወላጆቻቸዉ ተለይተዉና ትምህርታቸዉን ትተዉ ስራ ፍለጋ ወደ አረቡ አለም የሚጎርፉት እሱ ሊነግረን እንደሚፈልገዉ በአትራፊ ደላላዎች ተታልለዉ ወይም የአረብ አገር ኑሮ ጥሟቸዉ ሳይሆን ወያኔ በሚከተለዉ የዘረኝነት ፖሊሲና የተበላሸ የኤኮኖሚ ስርዐት የተነሳ መሆኑን ያዉቅ ይሆን? በተለይ ወጣት ሴቶቻችን በአረቡ አለም የሚደርስባቸዉን ዉርደትና መከራ እያወቁ በነጋ በጠባ አረብ አገር የሚሄዱት አገራቸዉ ዉስጥ ሰርተዉ መኖር ስላልቻሉ ከወያኔ ጋር ከመኖር አረብ አገር ሄዶ መሰንበት ይሻላል ብለዉ ነዉ አይናቸዉ እያየ የሞት ወጥመድ ዉስጥ የሚገቡት። ወያኔ በእጥፍ ድርብ አሳደግኩት የሚለዉ የአለማችን ፈጣኑ ታዳጊ ኤኮኖሚ ለእነዚህ ዜጎች የስራ ዕድል ፈጥሮ ቢሆንና ዜጎች ስራ የሚያገኙት ችሎታቸዉ ብቻ እየታየ ቢሆን ኖሮ ይህ ዛሬ የምናየዉ ብሄራዊ ችግርና ዉርደት አይኖርም ነበር። ይሉኝታና እፍረት የሚባል ነገር አብሮት ያልተፈጠረዉ ቴዎድሮስ አድሃኖም የዜጎቻችንን ወደ አረብ አገር መጉረፍ በደላሎችም ሊያሳብብ ሞክሯል። እሱ ለሚከስሳቸዉ ደላሎች የስራና የንግድ ፈቃድ ሰጥቶ በዜጎች ንግድ እንዲከብሩ መንገዱን ያመቻቸዉና የከፈተዉ የራሱ የቴዎድሮስ ፓረቲ ነዉ፤ ብዙዎቹ አትራፊ ደላላዎችም የራሱ የቴዎድሮስ ጓደኞች ናቸዉ። የቴዎድሮስ አድሃኖም ጉድ ብዙ ነዉ፤ ተዘርዝሮ አያልቅም።

ኢትዮጵያዉያን ወገኖቻችን ሳዑዲ ዉስጥ ሲጋዙና ሲገደሉ ቁጥሩ ተገኗል እያለ በወገኖቻችን ላይ ያፌዝ የነበረዉ ቴዎድሮስ አድሃኖም ነበር፤ ኢትዮጵያዉያን ወገንና ረዳት አለን ብለዉ ወደ ኤምባሲዉ በብዛት ሲመጡ ኤምባሲዉና ቆስንላ ጽ/ቤቶች በራፍ ላይ "ዝግ ነዉ" የሚል ጽሁፍ ለጥፎ ወገኖቻችንን ለባዕዳን ጥቃት አሳልፎ የሰጠዉ ቴዎድሮስ አድህኖም ነዉ፤የሳዑዲ መንግስት በአገሩ ዉስጥ ወንጀል ሲፈጸም ህጋዊ እርምጃ መዉሰድ መብቱ ነዉ ብሎ የወገኖቻችንን መገደልና የሴቶች እህቶቻችንን መደፈር ህጋዊ ለማድረግ የሞከረዉም ቴዎድሮስ አድሃኖም ነዉ። የሚገርመዉ ይህ ወገኖቻችንን በባዕድ አገር "አይናችሁን ለአፈር" ብሎ በሩን የዘገባቸዉ ከሃዲ ሰዉ ነዉ ዛሬ የወገን አሳቢና ደራሽ መስሎ ቀልዱ እንዳማረለት የመድረክ ላይ ኮሜዲያን እዚህም እዚያም ሽርጉድ የሚለዉ። ሳዑዲ ዉስጥ በወገኖቻችን ላይ ለደረሰዉ ይህ ነዉ የማይባል ትልቅ በደልና ጥፋት የኢትዮጵያ ህዝብ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ነጋሪቱም ተጎስሟል፤ ፋኖም ተሠማርቷል !!!

ዛሬ ኢትዮጵያዊያን እያዩ ያሉት ውርደት ቃል የሚገልፀው አልሆነም። ኢትዮጵያ በታሪኳ ዛሬ እየደረሰ ያለ ዓይነት ውርደት ደርሶባት እንደሆነ በታሪክ የተመዘገበ ነገርም ተፈልጎ አልተገኘም።ይሄ ለኢትዮጵያዊያን የጨለማ ዘመን ነው።በኢትዮጵያ እንዲህ ስደትና እንግልት፤ ሃዘንና ዋይታ የበዛበት ዘመን ታይቶ አይታወቅም።

በዚህ ግዜ በኢትዮጵያችን መንግስት ነኝ እያለ ራሱን የሚጠራ ቡድን አለ። ይሄ ቡድን አገሪቷን ከተቆጣጠረ ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያ የገባችበት የውርደት አዘቅት ከባድ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ በህወሃቶች አዝማችነት ተሰምቶ የማይታወቅ ጆሮን ጭው የሚያደርግ ግፍ በዜጎች ላይ ይፈፀማል።የተለየ የፖለቲካ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች ይዘው ግብረ ሶዶም እንዲፈፀምባቸው ያደርጋሉ፤ ሴቶች ልጆችን በጋራ ሁነው ይደፍራሉ፤ በተቀደሱ ስፍራዎች ገብተው ቅዱሱን ስፍራ ያረክሳሉ፤ ዜጎችን ከእርሻ ማሳቸው አፈናቅለው በገዛ አገራቸው መፃተኛ ያደርጓቸዋል። በአጠቃላይ ዜጎች በአገራቸው ተስፋ አጥተው ሃዘንተኛ እንዲሆኑ ያደርጋሉ። ተስፋ የቆረጡ ዜጎች ኢትዮጵያ ውስጥ ከምኖር ሂጄ ብሞት ይሻለኛል ብለው እግራቸው በመራቸው መንገድ ይሰደዳሉ። በእንዲህ ሁኔታ ከኢትዮጵያ በየዓመቱ ከ250ሺህ በላይ ወጣቶች ይሰደዳሉ። ገሚሱ በየበርሃው በውሃ ጥማት ወድቆ ይቀራል፤ ገሚሱም የባህር አዞ ቀለብ ሁኖ ዱካው ይጠፋል። ከሞት ተርፈው በየአርብ አገራቱ የደረሱ ዜጎች በሰው ልጆች ላይ ሊደርስ የማይገባ ወንጀል ይፈፀምባቸዋል። ባንዲራቸውን በአንገታቸው እንደጠመጠሙ ሬሳቸው ሜዳ ላይ ተጥሎ የአርብ መሳቂያ መሳለቂያ ይሆናሉ። በዚህ ሰሞን በሳውዲ ዓረቢያ እየተፈፀመ ያለው ግፍ ለኢትዮጵያዊያን ትልቅ ብሄራዊ ውርደት ሁኗል።

ይሄ በእንዲህ እንዳለ "መንግስት ነኝ" እያለ ራሱን የሚጠራው ህወሃት በዜጎቹ ሲቃና መከራ እየቀለደ ይገኛል። አንድ ግዜ ዜጎቼን እያወጣሁ ነው ይላል፤ ሌላ ግዜ ደግሞ የሥራ ፈቃድ የሌላቸው ስለሆኑ አላውቃቸውም ይላል። ህወሃቶች በዚህ ብቻ አላበቁም በኢትዮጵያዊያኑ ላይ እየተፈፀመ ያለውን ግፍ ለማስቆም አዲስ አበባ በሚገኘው በሳውዲ እምባሲ ፊት ለፊት ሠላማዊ ሠልፍ እንዳይደረግ መከልከል ብቻ ሳይሆን ለሠላማዊ ሰልፍ የወጡ ዜጎችን የቻሉትን ያክል ወደ እስር ቤት አግዘዋል፤ ያገኙትን ሁሉ በቆመጥ እንዲደበደቡ አድርገዋል። የአካል ጉዳትም አድርሰዋል። ይሄን ሁሉ ግፍ የሚታደግ፤ የህዝቡንም ሮሮ የሚሳማ መንግስታዊ አካል አልተገኘም። ዓለምም ፊቷን ያዞረችብን የሚመስል ሁኔታ ታይቷል።

ኢትዮጵያዊያን ቀና ብለን በኩራት በአርብ አገራት ጎዳናዎች ላይ የምንመላለስ ዜግች ነበርን። ስማችን ያማረ፤ ማንነታችን የተከበርን ዜጎች ነበርን።አረብ የሚያከብረን እንጂ እንዲህ የሚንቀንና የሚያዋርደን ዜጎች አልነበርንም። በዘመነ ህወሃት ግን ያ ሁሉ ክብራችን ተዋርዶ ዜጎቻችን እንደ ሌጦና ቆዳ በገንዘብ የሚሸጡ ሆኑ። በኢትዮጵያችን ላይ የነበሩ የቀድሞው ገዥዎች ምንም እንኳ ጨቋኞች ቢሆኑም ዜጎቻቸው በሌላ በማንም እጅ እንዲገላቱና እንዲዋረዱ የሚፈቅዱ አልነበሩም። በአንድ ወቅት አፄ ኃ/ስላሴን" ሠራተኛ ይላኩልኝ" ብለው የሳውዲው ንጉስ ሲጠይቋቸው "ለመሆኑ ምንድ ነው የምትፈልጉት መሃንዲስ ነው ወይስ ሃኪም" ብለው ይጠይቋቸዋል። አይ "እኛ የምንፈልገው በቤት ሠራተኛነት የሚያገለግሉንን ነው" ይላሉ አረቦቹ። አይ "እኛ ለቤት ሠራተኛ የሚሆን ዜጋ የለንም" ብለው መለስውላቸዋል። ለራሱም ሆነ ለወገኑ ክብር ያለው መሪ መልሱ እንዲህ እንጂ ሳውዲ ድረስ ሂዶ ዜጎቹን ለባርነት ለመሸጥ ሲዋዋል አይገኝም።

ደሳለኝ ኃ/ማሪያም ከስድስት ወር በፊት ሳውዲ ድረስ ገስግሶ ሂዶ የቤት ሠራተኞችን ለአረቦቹ ለመላክ ተዋውሎ መመለሱ የሚታወስ ነው። ይሄን ውል ሲዋዋል ግን ስለ ክፍያ፤ ስለ ዕረፍት ግዜ፤ በህመም ግዜ ምን ይሆናል የሚሉ መሠረታዊ ቁም ነገሮች በውሉ ውስጥ አልተካተቱም። በእነዚህ ነገሮች ምክንያት የኢንዶኔዥያ እና የፊሊፕልንስ መንግስታት ግን ምንም እንኳ ድሃ ብንሆንም ዜጎቻችንን የምንሰደው የታወቀ የክፍያ መጠን፤ የእረፍት ግዜ፤ የህመም ፈቃድ እነዚህንና ሌሎችን መሠረዊ ሁኔታዎችን በተመለከተ የተሟላ የህግ ድንጋጌ ሲኖራችሁ ነው። ይህን ህግ እስከምታበጁ ዜጎቻችን የእናንተ መጫወቻ እንዲሆኑ አንልክም ብለው እምቢ ማለታቸው ይታወቃል። ህወሃት መራሹ መንግስት ግን ስለውጪ አገር አኗኗር ምንም ዓይነት ግንዛቤ የሌላቸውን ወጣት ልጆችን ያለ ምንም ህግ ከለላ አሳልፎ ለባእዳን ይሰጣል። ወጣት ሴቶችንና ወንዶችን ለግርድናና ለአሽከርነት የመላኩ የድለላ ሥራም ህወሃቶች ባቋቋማቸው ድርጅቶች ተካሂዶ ከዚህ ንግድ በተገኘው ገንዘብ ህውሃቶች ብዙ ገንዘብ አፈሱ። ወገኖቻችን ግን በአረቦች እጅ እንባቸውን በመዳፋቸው የሚሰፍሩ ሆነው ቀሩ።

ለዚህ ሁሉ መከራ እና ውርደት ያበቃን ምንድ ነው የሚል ርዕስም የሰሞኑ የመወያያ ርዕስ ሆኗል። የመከራውና የውርደቱ ምንጭ ፈርጀ ብዙ ቢሆንም ህወሃት ዋነኛው የችግሩ ምንጭ ስለመሆኑ ብዙ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል።በአጠቃላይ ግን ህወሃት መንግስት ነኝ ብሎ ሲያበቃ ዜጎችን ለመታደግ ምንም ዓይነት ተግባራዊ እንቅስቃሴ አለማድረጉ ብቻ ሳይሆን ዜጎች በሰላማዊ ሰልፍ እንኳ ቁጣቸውን እንዳይገልጹ መከልከሉ ማንነቱን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። ለዚህ ብሄራዊ ውርደትና መከራ በመጀመሪያ ደረጃ ሊጠየቅ የሚገባው ህወሃት እንጂ ሌላ ማንም አይደለም። ህወሃት የኢትዮጵያዊያን ጠላት መሆንን የመረጠ የጠባብ ዘረኞች ቡድን ነው። ዜጎቻቸን እንዲህ ላለው ጉስቁልናና ውርደት እንዲጋለጡ ያደረጋቸው ህወሃት መሆኑን መያዝ ለነፃነት ለሚደረገው ትግል አንዱ አካል ነው።

### የተከበራችሁ ወገኖቻችን፤

በሳውዲ አረቢያ የሚሰቃዩ ዜጎችን በተመለከተ ህወሃቶች ምንም ተቆርቋሪነት ያሳዩበት ሁኔታ እንዳልታየ ታውቃላችሁ። ለወገን ተቆርቋሪነት ከህወሃቶች የሚጠበቅ ስላልሆነ እኛ አንደነቅም። አስቀድመው በገንዘብ አሳልፈው ለሸጧቸው ዜጎች ይቆረቆራሉ ብሎ መጠበቅ የህወሃቶችን ባህሪይ ካለመረዳት የሚመነጭ ብቻ ሳይሆን ህወሃቶች ዜጎች ማኩረፊያ አገር እንኳን እንዳይኖሯቸው የሚያሴሩትን ሴራ ለመረዳት ካለመፈለግ የሚመነጭም ጭምር ነው። ወደ አረብ አገር የተሰደዱም ሆኑ በሌሎች አገር በስደት ላይ ያሉ ዜጎች በከፋቸው ግዜ ተመልሰው የሚገቡበት ሥፍራ አላቸው ለማለት የሚያስደፍር ሁኔታ በኢትዮጵያ የለም። ጉራፈርዳ እና ቤንሻንጉል አገርህ አይደለም ተብሎ የተባረረ ወጣት መግቢያው የት ነው? ከዚህ ሥፍራ ወደ ሳውዲ የተሰደደ ወጣት መመለሻው ወደየት ነው? በዚያች አገር ድንጋይ ለመፍለጥ እንኳ የኢሕአዴግ አባል እንዲሆን በሚገደድበት አገር ምን አገር አለኝ ብሎ ነው የከፋው ወደ ኢትዮጵያ የሚመለሰው ? አዎን ኢትዮጵያዊያን ማኩረፊያ አገር የሌለን ከርታታ ዜጎች እንድንሆን ተደርገናል።አገር ያሳጡንም ህወሃቶች ናቸው እንጂ ሌላ ማንም አይደለም።

### እንግዲህ ምን ይደረግ?

ይሄ ጥያቄ ግልጽና ቀላል መልስ አለው። አምርሮ መነሳት። ህወሃቶች በአዲስ አበባ ላይ ወንድ ልጅን አስገድደው ግብረ ሶዶም እንዲፈፀምበት ሲያደርጉ ሰምቶ "እነዚህ ምን ዓይነት አረመኔዎች ናቸው" ማለት ብቻ በቂ አይደለም። ለአረመኔ የሚገባውን ቅጣት ለመስጠት የአያቶቻችንን ጋሻና ጦር ማንሳት ግዜው የሚጠይቀው ታሪካዊ ግዴታ ነው።በሳውዲ አረቢያ በወገኖቻችን ላይ እየተፈፀመ የቆየውን ውርደት እንምባ ብቻ የሚያስቆመው አይሆንም።እንዲህ የአረብ መቀለጃ የሆነውን ማንነታችንና ክብራችንን አስመልሰን አንገታችንን ቀና አድርገን በአርብ ጎዳናዎች ላይ እንደቀድሞው ዘመን በኩራት እንድንመላለስ የአያቶቻችንን ትጥቅ ከተሰቀለበት አውርደን መታጠቅ ግዴታችን ሁኗል።

ግንቦት ሰባት ንቅናቄ ውስጥ ያለን ኢትዮጵያዊያን በወገኖቻችን ላይ እየተፈፀመ ያለው ውርደት ብሄራዊ ውርደት ነው እንላለን። ከዚህ በላይ ሌላ ብሄራዊ ውርደት የለም። ለዚህ ውርደት ያደረሰንም ህውሃት ነው። ህወሃት እስካለ ድረስ ብሄራዊ ውርደታችን ይቀጥላል እንጂ አይሻሻልም። እኛ የሚደርስብንን ውርደት ለማስቆም አምርረን ተነስተናል። እኛ እንዲህ ተዋርደን መኖርን ከቅድሞዎቹ ኩሩዎች አያቶቻችን አልተማርንም። እኛን ባንዳዎችና የባንዳ ልጆች ህወሃቶች አንገታችንን አስደፍተው አዋርደው አይገዙንም። አያቶቻችን ለነፃነታቸው እና ለአገራቸው ክብር ሲሉ በቆሙበት በጀግኖች ሥፍራ ለመቆም መንገዱን ጀምረናል። ከእንግዲህ ወዲያ ከዚህ ጉዞ የሚያቆመን ምንም ዓይነት ምድራዊ ኃይል የለም። ለእኛ ነጋሪት ከተጎሰመ ቆይቷል እኛ የነጋሪቱን ድምፅ በሰማን ግዜ ሳናቅማማ ተነስተናል።

እናንተስ ሳትቅማሙ ለመነሳት የነጋሪቱን ድምፅ ሰምታችኋል? ከወደ ሳውዲ የተሰማው ያ የሲቃ ጩኸት፤ ያ ሮሮ፤ ያ እንምባ አስደንጋጩ የነጋሪት ድምፅ ነው። ከዚህ ድምፅ በኋላ ፋኖ ይሠማራል እንጂ አያለቅስም። ማልቀስ የናቁንና ያዋረዱን እንዲያከብሩን አያደርግም። ነጋሪቱ ከተጎሰመ በኋላ አገሬን፤ ክብሬን የሚል ተነስቶ ያያቶቹን ጋሻና ጦር ያነሳል እንጂ እንዲያው ዝም ብሎ አያጉረመርምም። አገር ተዋርዳ፤ ህዝብ ተበደሎ ዝም ብሎ ተንጋሎ የሚተኛ ካለ ይህን ብሄራዊ ውርደት ካመጡ ቡድኖች በምን እንደሚለይ ራሱን ይጠይቅ። አበቃን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!!**

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ማን ነው የተዋረደው?

ይሄይስ አእምሮ ( ክፍል 1 )

ከጥቂት ሣምንታት ወዲህ በተለይ የኢትዮጵያን የወያኔ መንግሥት በሚቃወሙ የሚዲያ ማዕከላት ዘንድ ዋና መነጋገሪያ ሆኖ የሚገኘው በሳዑዲ የኢትዮጵያውያን መንገላታትና መሰቃየት እንዲሁም ከኢሰብኣዊነትም በወረደ ሁኔታ በግፍ መጨፍጨፍ ነው። ዜጎቻችን በአካፑልኮ ቤይ የመዝናኛ ሥፍራ ሲንሸራሸሩ ከርመው የመጡ ይመስል ይህ ምስል በኢትዮጵያው የወያኔ ሚዲያ በአስደሳች መልክ እየቀረበ ቢሆንም ትክክለኛውን መረጃ ከአማራጭ የዜና ምንጮች እንደወረደ እንደምንከታተለው ከሆነ ግን ከሀገርና ከሕዝብ ኅልውና አኳያ ነገሩ እጅግ አሳሳቢ ነው። ከአንድ ጨለማ ውስጥ ብርሃን እንደሚጸነስ ሁሉ ከዚህ አስከፊ ገጠመኝ ውስጥ የፈነጠቀው የሕዝብ አንድነት ግን በሌላ ወገን ተስፋችን እንዲያንሠራራ አድርጓል። ፈረንጆቹ “blessing in disguise” ወይም “mixed blessing” እንደሚሉት ይህ መጥፎ አጋጣሚ ሊረሳ የተቃረበውን የሕዝብ አንድነት በማደስ በመላው ዓለም የተበተነው ኢትዮጵያዊ በአንድነት ቆሞ ድምፁን እንዲያሰማና ለጋራ ኅለውናው እንዲያለቅስ አስችሎታል። በተመሳሳይም የሕዝቡ ስሜትና እውነተኛ ፍላጎት በየስብሰባዎቹና ሰላማዊ ሰልፎቹ ሲንጸባረቅ እንደተመለከትነው ወያኔን ከመሰሉ በርካታ ከፋፋይ የዘር ፖለቲከኞችና የሃይማኖት ቡድኖች ሸረኛ ሤራ ባፈነገጠ መልኩ በአንድ ሉዓላዊ መንግሥትና በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ሥር የመኖር የቆዬ ኢትዮጵያዊ አብሮነቱን የታዘብንበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በሌላ አቅጣጫ ደግሞ በዚህ ስቃይ ለማትረፍ የሚፈልጉ በተለይም ወያኔዎችና መሰል ልበ ደንዳናዎች ለምርጫ ዝግጅት በፕሮፓጋንዳነት ሲጠቀሙበት፣ ለገቢ ማግበስበሻም ከማዋል እንደማይመለሱ እየተነገረ ነው።

ከጓደኞች ጋር ስንወያይ አንዳንዶቻችን ይህ ነገር በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ ብቻ የተነጣጠረ ሣይሆን በአጠቃላይ በሰው ልጅ ኅልውና ላይ የተቃጣ ታላቅ የክፍለ ዘመኑ ወንጀል መሆኑን ተገንዝበናል። ስለዚህ ማፈር ያለበት ነጭ ጥቁር ሳይል የሰው ልጅ በአጠቃላይ እንጂ ኢትዮጵያውያን ብቻ አይደሉም ወደሚለው እሳቤ አዘንብለናል። አንድ የዓለም ዜጋ በመጥቆር በመንጣቱ ወይም በመክበር በመደኸየቱ፣ በዚህ ወይ በዚያ ዘውግ አባልነቱ፣ በዚያ ወይ በዚህ ቋንቋ ተናጋሪነቱ፣ ወይም በመስለምና ባለመስለሙ፣ በክርስትና እምነትም በመጠመቁ ወይ ባለመጠመቁ ሣይሆን በኢትዮጵያዊነቱ ብቻ እንዲህ ዓይነት ዘግናኝ ግፍ የሚደርስበት ከሆነ ነግ ከነግ ወዲያ ታሪክ ሲለወጥ ይህ ዓይነቱ ውርጅብኝ በማንም ሌላ ወገን ላይ እንደማይደርስ ማንም ዋስትና ሊሰጥ አይችልም። ዛሬ በኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰው ዕልቂት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በአይሁዶች ላይ ከደረሰው ቢበልጥ እንጂ አይተናነስም፤ አሁን በኢትዮጵያውያን ላይ በሀገራቸው ውስጥም ሆነ ከሀገራቸው ውጭ እየደረሰባቸው የሚገኘው ዕልቂት ሩዋንዳና ዩጎዝላቪያ ወይም ኢራቅና አርመን ውስጥ ከደረሰው ጭፍጨፋ ቢብስ እንጂ አያንስም። መነሻ ምክንያታቸው የሚለያዩ ግን ይበልጡን ከኢኮኖሚ ጥቅምና ከዓላማ ቁርኝት ጋር የሚያያዙ የሰው ዘር ፍጅቶች በየዘመናቱ በብዙ ሀገራት ተፈጽመዋል፤ አሁንም ድረስ በመፈጸም ላይ ናቸው። ነገር ግን ግንዛቤ ያላገኘው ነገር በአንዱ ላይ የሚፈጸመው ነገር በሌሌላው ላይ እንደተፈጸመ ያለመቁጠር ነው። ይህ ትልቅ ዓለም አቀፍ ችግር ነው። በአንድ የየትኛውም ሀገር ዜጋ ላይ የሚደርስ ችግር በማንኛውም የሰው ልጅ ላይ እንደደረሰ ችግር ካልተቆጠረ በሰው ልጆች አጠቃላይ አስተሳሰብ ላይ የተዛባ ነገር አለ ማለት ነው። ይህ የተቃወሰ አስተሳሰብና አመለካከት መፍትሔ ካላገኘ የሰው ልጅ በውድቀት መንገድ እንደነጎደ ይቀጥላል ምፅዓቱንም ያቃርባል እንጂ ዓለማችን ወደተሻለ ኅሊናዊና ቁሣዊ የዕድገት ጫፍ አትደርስም። **yiheyisaemro@gmail.com**

( ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል )

## ፋሽስት ወያኔ ከምንም በላይ የዜጎቻችን ደህንነት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ወያኔ እንደፈለገ አጣሞ የሚተረጉመው ፖለቲካ ሰብአዊ መብቱን ተጠቅሞ መናገርና መጻፍ ለጀመረው ሁሉ የመከራ ጊዜ እየሆነበት ስደትን እንደአማራጭ መውሰዱ ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ መገለጹ የሚታወቅ ቢሆንም ቴወድሮስ አድሃኖም ግን ሁሉንም የፋሽስት ወያኔ ጥፋቶች ወደደላሎችና ኤጀንሲዎች ማስተላለፉን መርጧል።

የአዲስ አበባውን ሰላማዊ ሰልፈኛ ለመበተን ጥይት የተጠቀምነው ሰልፈኛውን ለማባረር የሚያገለግል ውሃ መርጭያ መኪና ስላልነበረን ነው በማለት ወያኔ ሲያሾፍ እንደነበር የሚያስታውሱ ወገኖች፤ ባንድ ቃል፣ ከሕዝባችን እንጅ ከወያኔ ምንም የሚተበቅ ነገር የለም፤ ተባብረን በመስራት ወያኔን እናስወግድ ማለታቸው ተያይዞ ተጠቅሷል።

## በጅጅጋ የብሄር ብሄረሰቦችን ቀን ለማድመቅ የተቀረጸው

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የዘንድሮዉን የብሄርቤረሰቦች ቀን ለማክበር ኦጋዴን ክልል ስቴዲየም በመገንባት ላይ የተጠመደው ሲሆን፤ ክልሉ በገጠመው ከፍተኛ የበጀት እጥረት የተነሳ በዐሉ የሚከበረዉ ገና በመሰራት ላይ ባለ ስታዲየም ዉስጥ መሆኑን ከጅጅጋ የደረሰን ዜና ያመለክታል። የፌድሬሺን ምክር ቤት ባካሄደው ግምገማ ከ10 ሚልየን ብር በላይ ገንዘብ ያለ አግባብ የባከነ መሆኑን አረጋግጦዋል። በተመደበው በጀት ዘወትር ከስራ ስዓት ውጭ የከስዓት ጊዜን በመጠቀም የክልሉ ባለስልጣናት ገንዘቡን ጫት ቅመውበታል ሲል ምክር ቤቱ ትችት አቅርቧል። ለበዓሉ ዝግጅት የተመደበለትን 31 ሚልዩን ብር ከዝግጅቱ በፊት ቀድሞ ያጠናቀቀው የሶማሌ ክልል መንግስትን ለበአሉ ማክበሪያ እና ማድመቂያ በማለት ተጨማሪ 14 ሚሊዮን ብር ጠይቋል።የፌዴሬሺን ምክር ቤት በበኩሉ የተለያዩ ባለስልጣናትና አርቲስቶች የሶማሌ ክልልን ለማስጎብኝት በሁዱበት ወቅት ለመጓጓዝያ እና ለመስተንግዶ 200 ሚልየን ብር ወጭ አውጥቻለሁ ብሏል። ለህዳር 29ኙ በአል ከተዘጋጁ ባነሮች መካከል ባቡር፤ አባይ ግድብ ፤ ቤቶች እና ህገ መንግስት ይገኙበታል። ይህ ባነር ለህዝብ ተደብቆ ከቆየ በኃላ በህዳር 28 ይመረቃል።

## ግንቦት7 እና አክራሪ ኃይሎች ፓርላማውን ተቆጣጥረዉ ሊጎዱን . .

( ከገጽ 1 የዞረ )

በቀጣዩ የምክር ቤት አባላት ምርጫ ኢህአዴግ የሚያገኘዉ ወንበር ግንቦት ሰባትና አክራሪ የእስልምና ሀይሎች በኢህአዴግ አባላት ስም በሚያቀርቧቸዉ እጩዎች ሊነጠቅ ይችላል። ሽፈራው ተክለማርያም እዚህ ድምደሜ ላይ የደረሰዉ የምርጫ 97ትን ዉጤት ከገመገመ በኋላ እንደሆነ ተናግሯል። በ1997ቱ ምርጫ ወቅት ቅንጅት ላገኘዉ ከፍተኛ ዉጤት ምክንያት የሆኑት የኢህአዴግ አባላት ሆነው ዉስጥ ዉስጡን ለቅንጅት ይሰሩ የነበሩ ሰዎች እንደነበሩ ሽፈራው ተክለማርያም በንግግሩ ዉስጥ ጠቀስ አድርጎ አልፏል።

በክርስትና ሀይማኖት በኩል በተደጋጋሚ የሚሰማዉ “መንግስት በሃይማኖት አባቶች ሹመት ላይ እጁን ያስገባል፤ የዋልድባ ገዳም ተደፈረ፤ አብያተክርስታያናት እየተባለ የሚወራዉ ወሬና ይህን የሚያባብሱ ኢሳትና ቪኦኤን የመሳሰሉ ሜድያዎች መኖር የውጭ ሚዲያ መኖር ጉዳዩ ትኩረት እንዲያገኝ ማድረጉን ሽፈራው ተክለማርያም ተናግሯል።የሙስሊሙ እንቅስቃሴ በተመለከተም ሽፈራው ተክለማርያም ሲናገር ከቅንጅት እስከ ህብረት፣ ከቪኦኤ እስከ ቲቪ አፍሪካ፣ ከጀርመን ድምጽ እስከ ቢላል ሬዲዮ፣ ከጅሃዳዊ ሀረካት እስከ ግንቦት ሰባት፣ ከኢትዮጵያ ሙስሊሞች ዓለም አቀፍ እስከ መድረክ እስከ ስደተኛው ሲኖዶስ ያሉ ሀይሎች በተናጠልና በህብረት” ተሳትፈውበታል ብለዋል። የኢትዮጵያ ሙስሊሞች እንቅስቃሴ የተዳከመ የመሰለዉ ተላላዉ ሽፈራው ተክለማርያም የሙስሊሙ እንቅስቃሴ በከፍተኛ ፍጥነት የመዳከም ሂደት ውስጥ የገባው በቡድኑ ቀንደኛ መሪዎች ላይ ህጋዊ ስርአቱን ተከትሎ የእስራት እርምጃ ከተወሰደ በኋላ ነው ሲል አገዛዙንና እራሱን ለማጽናናት ሞክሯል።

በሃይማኖት ሽፋን የሚካሄዱ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውለው አድረው እየተጋለጡና እየተዳከሙ መሄዳቸው ባይቀርም ባለፉት ሁለት ዓመታት ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱን በሀይል ለመፈታተን ከሞከሩት የሁከት ሀይሎች ዋነኞቹ ነበሩ ያለዉ ሽፈራው ተክለማርያም “በሃይማኖት ስም የሚካሄደውን ንግድ ውጤታማ እንዲሆን በማድረግ ረገድ የድህነት መንሰራፋትና የመልካም አስተዳደር እጦት ወይም ጉድለት ተጠቃሽ ናቸው፤ በተለይ ከድህነትና ኋላቀርነት መውጫውን ትክክለኛ መንገድ የሚያመላክት መሪ ድርጅት በሌለበት ቦታ፣ በሃይማኖት ሽፋን የሚነግዱ የፖለቲካ ሀይሎች አንዱን በሌላው ላይ ማነሳሳት የፅድቅ መንገድ እንደሆነ አስመስለው በማቅረብ ዜጐችን ወደጥፋት ይመራሉ” ብሏል። አንደ ሽፈራው ተክለማርያም አባባል መሪ ድርጅት ቢኖርም ህዝብን ለአንድ አላማ ማሰለፍ የሚችል መሪ በሌለበት ሁኔታ ችግሩ ተባብሶ መቀጠሉ አይቀርም። አሁንም ድህነትና ኋላቀርነት በመኖሩ፣ በፓርቲና በመንግስት አመራራችን የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ጉድለቶች በመኖራቸውና የእምነት ጉዳይ ለሚዛናዊ አስተሳሰብ ያለው ተጋላጭነት ዝቅተኛ በመሆኑ አልፎ አልፎ የተካረረ ፍጥጫ እያጋጠመ መሆኑንም ሽፈራው ተክለማርያም በጥናታዊ ጽሁፉ ዉስጥ በግልጽ አስቀምጧል።

## ቴዎድሮስ አድሃኖም ቢያጥቡት የማይጠራ . . .

( ከገጽ 1 የዞረ )

ከሚያደርጋቸዉ የወያኔ ባለስልጣኖች ዉስጥ ቴዎድሮስ አድሃኖምና ተላላኪዉ ዲና ሙፍቲ የመጀመሪያዎቹ ናቸዉ።

ከሰሞኑ ፊቱን እያሳመረ በየደቂቃዉ ኢቲቪ ላይ መቅረብ የጀመረዉ ቴዎድሮስ አድሃኖም “ሳዑዲ ዉስጥ ለደረሰዉ ጥፋት መንግስት ተመጣጣኝ እርምጃ ይወስዳል” እያለ ሲዘለብድ ተሰምቷል፤ የሱ ተላላኪ የሆነዉ ዲና ሙፍቲ ደግሞ “በዜጎች ላይ ምን ግዜም ድርድር የለም” ብሎ ሲናገር ተደምጧል። ይህንን በሁለት ባዶዎች የተነገረ ባዶ ንግግር ያዳመጠ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን “ጽድቁ ቀርቶበኝ በወጉ በኮነንከኝ” እያለ የቴዎድሮስንና የዲና ሙፍቲን “ጅብ ከሄደ ዉሻ ጮኸ” ንግግር ሰምቶ እንዳልሰማ አልፎታል። የሚገርመዉ ይህ ወገኖቻችንን በክፉ ቀን ወግዱ ብሎ ፊቱን ያዞረባቸዉ ቴዎድሮስ አድሀኖም ነዉ ዛሬ የሳዑዲ መንግስት በራሱ ወጪ አዲስ አበባ የሚልካቸዉን ዜጎች ዘመድ መስሎ ለመጠየቅ የሚሄደዉ። ደግሞኮ እስከዛሬ ድረስ አዲስ አበባ ገብተዋል የሚባሉት በጣት የሚቆጠሩ ሰዎችም ቢሆኑ በተለመደዉ የወያኔ የዘመድ አሰራር እየተመረጡ የመጡ እንጂ ዜግነታቸዉ፤ ዕድሜያቸዉና የጤንነት ሁኔታቸዉ እየታየ የተመረጡ ሰዎች አይደሉም። ባጠቃላይ የተጣለበትን አገራዊ አደራና የተሰጠዉን ህዝባዊ ሀላፊነት መወጣት የተሳነዉን ቴዎድሮስ አድሀኖምን በየሜድያዉና በተገኘዉ አጋጣሚ ሁሉ እያሽሞነሞኑ ለማቅረብ የሚደረገዉ ጥረት እንደ ህፃን ልጅ ሽንት መቀበያ የቆሸሸዉን የወያኔ ፊት በቆሻሻ ዉኃ ከማጠብ ተለይቶ የሚታይ አይደለም። ወያኔ ከአሳማ አሳማ እየመረጠ ለማሳመርና ለማሽቀርቀር የሚያደርገዉ ጥረት አሳማዉን ወደ ለመደዉ ወደ ጭቃዉ ዉስጥ ይበልጥ ይስበዋል እንጂ በፍጹም አያሳምረዉም፤ ምክንያቱም አሳማ አጌጥነዉ አላጌጥነዉ ምን ግዜም አሳማ ነዉ። የቴዎድሮስ አድሃኖም ነገርም እንደዚሁ ነዉ፤ ወያኔ ያሻዉን ያክል ቢቀባዉና ቢያሳምረዉ ቴዎድሮስ አድሃኖም ወያኔነቱን አይለቅም! ወያኔ ደግሞ በልቶ የማይጠግብ ታጥቦ የማይነጻ አሳማ ነዉ።

**ebini23@yahoo.com**